# ይህ የሕዝብ ትግል መጥራት አለበት

ከፈትበር

ካለፈው ምርጫ በፊት የህዝቡና የጠላት ጎራ ለይቶ ፍልሚያውም በኢላማው ላይ አነጣጥሮ ሲካሄድ እንደነበር ዛሬ እንዳታሪክ የምናወራው ነገር ሆንኗል። ወያኔ ባንድ ወገን በህዝቡ የታቀፉ ድርጅቶች ደግሞ በሌላ ወገን ቁመው ወያኔን ሲፋለሙ አይተናል። የሚያሳዝነው ግን ይህ ሃቅ ዛሬ ታሪክ ሆኗል። ተንጦ ተንጦ ሊወድቅ በጣር ላይ የነበረውን ወያኔ ዛሬ በተገላቢጦሹ ያማረበት ጎብዝ መስሎ ይታያል። ሲፈልገው ያስራል ሲፈልገው ይፈታል። ያውም ማረኝ ካልተባለ ወይፍንክች ብሏል። ይህን የልብ ልብ ወያኔ ኬት አመጣው? መልስ የሚሻ ጥያቄ ነው።

ትግል ምንጊዜም ቢሆን መራራ መስዋእትነትን እንዳሚጠይቅ ከቲዮሪውም ከተግባሩም ተምረነዋል። ትግሉ ውጣውረድና ጠመዝማዛ ነው ስንል የጠላት ዘዴ መቀያየርና በቀላሉ ያለመሸነፉን ለመጠቆም ነበር። የፖለቲካው ሳይንስ የሚለው የህዝቡ ወገን የትግል ስልት ጥራትና ጉልበት እያገኘ የሚያድገውን ያህል ጠላትም የዚያኑ ያህል በአጥፊ ተንኮሉ መዳበሩ የማይታበል ነው። ኢሕአፓ ያለውን ደርግ ጠምዘዝ አድርጎ ያቀርብ እንደነበር ያየነው የቅርብ ጊዜ ታሪክ ነው። ኢሕአፓ ስለ ሶሻሊዝም ሲያወራ ደርግ ደግሞ የኢትዮጵያ ትቅደም ሶሻሊዝምን ሰብኳል። ኢሕአፓ ስለመሬት ላራሹ ሲታገል ደርግ መሬቱን ለባለመሬቱ መለስኩ ብሏል። የኢሕአፓን በሕዝብ ተወዳጅነት ለማርከስ ኢሕአፓ ከሱማሌ ጎን ሆኖ ወጋኝ ማለቱንም እናስታውሳለን። ለመጠቆም የፈለኩት የሕዝብ ሃይል ሲያይል የጠላትም ሃይል እንደሚበረታ ነው። ግን ዘላቂ አይሆንም። መቀመቅ መግባቱ አይቀሬ ነው።

ሊወድቅ አንድ ሐሙስ የቀረው ያ የትናንትናው ወያኔ ዛሬ ያገኘውን ወኔ ከየት አመጣው? ወያኔ የህዝብ ድጋፍ የለውም። የወያኔ የኢኮኖሚ ፖሊሲ ሕዝቡን በረሃብ እያሰቃየው ነው። የወያኔ የውጭ ፖሊሲው ከመበላሸቱም በላይ የአገር ድንበር ዘሎ የራሱን ወታደር እያስፈጀና ጠላት ብሎ የፈረጀውንም ህዝብ በቻለው መሳሪያ ሁሉ ለማጥፋት ሌት ተቀን እየታገለ ይገኛል። ጎበዝ የተቃዋሚውን ጎራ ምን ነካው? ሌላው ቢቀር ገና እንዳትግል ጀማሪ በወረቀት እንኳን የወያኔን ሴራ ማጋለጡ ተስኖን ሲታይ የምን አፍዝ አደንግዝ ወረደብን ብሎ መጠየቁ ተገቢ ይመስለኛል።

የሚጠራጠር ካለ ጥናት ያድርግ። የማያምን ካለ አይኑን ይክፈት። ወገን ዛሬ ትግላችንን ወደ ኋላ እንደ ግመል ሽንት የሚጎትት ተላላፊ ተውሳክ በህዝባዊ ድርጅቶች ውስጥ ገብቷል። ይህ ተውሳክ አንጃ ይባላል። ልደቱ ከቅንጅት ሲኮበልል ያያዘው ተውሳክ አንጃነት ነበር። ይተላለፋል። ይበክላል። የህብረቱም ሁለቱ ዶክተሮች ከአንጃነት ልክፍት አላመለጡም። ወያኔ ማገገም የጀመረው ያኔ ነበር። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ይህ ዝባዊው ጎራ አልቀናውም። ይህ የህዝብ ጎራ ሰኔና ሰኞ የገጠመበት ይመስላል። ጎብዝ ይህ የሕዝብ ትግል መጥራት አለበት።

የነልደቱ አንጃ ቶሎ ጎልቶ ወጣ እንጂ ኢሕአፓን ሲቦረቡር የነበረው አንጃ የተያያዘውን የመቦርቦር ተልእኮ እስኪያጠናቅቅ መደበቅ ነበረበት። ዛሬ ያዙኝ ልቀቁኝ የሚለው ከኢሕአፓ የፈረጠጠው አንጃ የጥፋት ተልእኮው ስር የሰደደ ነበር። የወዳጅ ጠላትን ቶሎ መለየት በጣም አስቸጋሪ ጉዳይ ነው። ላመታት አብረውን ግን እንደመዥገር የድርጅቱን ደም እየመጠጡ ሲያመነምኑን ነበር። ወያኔ ደግ ሆኗል ገብተን በሰላም እንታገል ብለውን እንኳን ሲጋልቡን የ ቃት ቋታቸው የጎደለ መስሎን ተሃድሶ ለማድረግ ተሞክሯል። ካለፈው ታሪካችን መማር ተስኖን በብተናው ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርገው አሜሪካ ገብተው ሌላው አባል ህዝባዊ ትግሉን ገፍተ እያሉ የራሳቸውን ኑሮ አስተካክለው ብቅ ያሉት ጉዳኛውን ሰው መሪ አድርገን “ባልወለደ” አንጀታቸው ድርጅታችንን ሲገዘግዙ ከረሙ። ከቦታ ቦታ እየተዘዋወሩም ተክለ-ሰውነት ለመገንባት ያልተዋጣ ዘመቻ ላመት አካሄዱ። “ኢሕአፓ ጠፍቷል ወርሃዊ መዋጮ የምታወጡት በከንቱ ነው።” በማለት የአባላቱን ወኔ ለመስለብ ብዙ ደክመዋል። የድርጅቱን ሚስጢር ለኢትዮ ሪቪው ድህረገጽ በመላክ ኢሕአፓ አበቃለት ብሎ እንዲጽፍ ካዘጋጁ ጋር አሲረዋል።

ኢሕአፓ ከወያኔ ጋር የሚያካሄደውን ፍልሚያ ሙሉ በሙሉ እንዳይወጣ አንጃው ተብትቦ ለዘመናት ያዘውው። ተጋልጠው ከድርጅቱ ጉባኤ ረግጠው እንደወጡ ከወያኔ ባልተናነሰ ጉልበት ኢሕአፓን ለማጥፋት ዛሬ እየተራሯጡ ይገኛሉ። ኢሕአፓ ከወያኔ ሲፋለም አንጃው ከኢሕአፓ ጋር የሞትና የሽረት ትግል እያደረገ ይገኛል። ወያኔም ይህን የጅ መንሻቸውን እንደሚባርክላቸው የቅንጣት ያህል ልንጠራጠር አይገባም።

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

የቋመጡትማ ኢሕአፓን ሙሉ በሙሉ ለወያኔ የማይጎረብጥ ስጦታ በማድረግ ከወያኔ የስልጣን ትራፊ ለመሻትም ነበር። እድሜ ለሃቀኛ የኢሕአፓ ልጆች የአንጃው ሴራ ፍርክስክሱ ወጣ!!

ድርጅቱን መልቀቅ መብታቸው ነው። ካልጠፋ ስም ግን የህዝብ የሆነውን የድርጅት ስምና ልሳን አለቅም ማለት ህዝቡን ለማደናገርና ለወያኔ የልብ ልብ መስጠት ይሆናል። ኅበዝ ይህ አንጃ እድሜ ካገኘ ልሳናችን በሆነው ዲሞክራሲያ ላይ መለሰን ጀግናው መሪያችን ብሎ ቢያወጣ እንዳትደነግጡ ካሁኑ ማሳሰቡ ተገቢ ይመስለኛል። ወያኔ አትበሉ ስሙ ኢህአዴግ ነው ብለው አስጠንቅቀውናል። ወደ ወያኔ ጠጋ ጠጋ ማለቱ ከእለት ወደ እለት በመጠንከር ቀጥሏል።

ያንጃው በሽታ ወደ ህብረቱም ዘልቆ ገብቷል። አንጃው ኢሕአፓ ማለት እኔ ነኝ ተቀበሉኝ ብሎ ሲጠይቅ ድጋፍ የሰገሱት አንዳንድ የህብረቱ አባላት እንዳልጠፉ ከደገፉት ወገን ጓዶቻቸው በስማ በለው ሰምተናል። በነገራችን ላይ ህብረቱ ጠንክሮ እንዲታገል ያላሳለሰ የገንዘብና የጊዜ አስተዋጽኦ ያደርጉ የነበሩት የኢሕአፓ አባላት ስለመሆናቸው ማንም የሚስተው አይደለም። አንጃው ስሙን ቀይሮ የህብረቱ አባል መሆን ይችላል። ይህን መብታቸውን ኢሕአፓ ያከብርላቸዋል ብየ አስባለሁ። ያንጃው ተልእኮ የህዝቡን ትግል መበረዝ ማደናገር በመሆኑ ይህን አይቀበልም። ልክ ኢሕአፓን በማወክ ጸረ ወያኔ ትግሉን ለመስለብ እንደሚያደርገው ሁሉ ህብረቱንም ቀፍድዶ በመያዝ ትግሉ ርስ በርስ እንዲሆን አድርጎታል። ለመሆኑ ህብረቱ ጋዜጣዊ መግለጫ ካወጣ ስንት ወራት አለፉት? ኢሕአፓም እኮ ባንጃው ተወትሮ ባለበት ወቅት ባመት ያወጣው ቢበዛ ሁለት ይመስለኛል።

ቅንጅትም ተመሳሳይ ወረርሽን እንደገባበት ለህዝቡ ማርዳት ድካም ነው ትርፉ። ጸሃይ የሞቀው ሃቅ ነውና። የሚገርመው ግን ይህ የኢሕአፓ አንጃና የቅንጅት አንጃ ገና ከመሰረታቸው የውስጥ ለውስጥ ግኑኝነት እንደነበራቸው የውስጥ አዋቂዎቻችን ይነግሩናል። በቅርቡ የራሳቸው የሆነ የጋራ ግንባር እንደሚያውጁም ተደርሶበታል። ግንባሩ ወያኔን በማያስከፋ መንገድ እንደሚሆን ሳይታለም የተፈታም ነው። በዚህ በዲያስፖራው ያለው አንጃ ምናልባትም ካሜርካ ቅባቅዱሱን ካገኘ በኋላ ካገር ቤቱ ወዳጅ አንጃዎች ጋር ግንባራቸውን እንደሚያጠናክሩ ይጠበቃል። ምርጫ 2010 ላይም እንደሚሳተፉ የዛሬ አመት ገደማ የያኔው አስመሳይ ኢሕአፓ የዛሬው የአንጃ መሪ ካናዳ ላይ የወያኔ ከፍተኛ ያመራር አባል በተገኘበት ሰብስባ ላይ ይፋ አውጥቶታል። ይህ ስብሰባ ተደብቆ የነበረውን የኢሕአፓ አንጃ ግልጽ ያወጣው ነበር።

ኅበዝ ይህ የተያያዝነው የትግል ዘዴ መጥራት ይገባዋል። ቅንጅቱም ሆነ ህብረቱም እንደዲሬቶ ሲጣጣፉ የሚዘልቁ አይመስለኝም። እንደ ደፈረሱም መቀጠል የለባቸውም። ቅንጅቱ ለሁለት ተከፍሎ ህብረቱም ወዳጁንና የጀርባ አጥንት የሆነውን ኢሕአፓን በአንጃ መለወጥ አይጠበቅበትም ከሆነም የሚጎዳው ህብረቱ እንጂ ኢሕአፓማ ከጂዎቹን አሳፍሮ በድል ከህዝቡ ጋር ብቅ ይላል። የሌላውን ብዙም ባላውቅም ከኢሕአፓ የወጣው አንጃ አኳን ግን ለህዝብ ሊቆረቆር ቀርቶ ለራሱም የማይሆን ጊዜው የከዳው ስብስብ ነው። የሞራልም ድክመት ያለባቸው ያደሩበትንና የበሉበትን ወጭ የሚክዱ ስለመሆናቸው ካለፈው ልዩ ጉባኤ ብዙ ገምግመናቸዋል ። ችግራችን ለምን አጭበረበሩን ሳይሆን ለምን ከወያኔ ጋር የምናደርገውን ትግል ለማበላሸት ይሞክራሉ ነው።

የወረረንን ያንጃዎችን ቅጽፈት ባስቸኳ ፈውስ መስጠት አለብን። ያለበለዚያ የህዝቡን ትግል መራራና የተራዘመ ያደርጉታል። ህዝባዊ በመምሰልም ትግሉን ሽብበው የወያኔን እድሜ ያራዝሙታል። በዚህ ፈታኝ ወቅት ስህተት እንኳን ቢኖር ስህተቱን ለማረም መረባረብ እንጂ የህዝብ አለኝታ የሆነውን ቆራጥ ታጋይ ድርጅት መሰንጠቅ ወያኔን ከመጥቀም ወዲያ ለህዝብ ልንታገል ነው ቢሉን የሌባ አይነደርቅ ከመሆን ወዲያ ምን ሊባሉ?

ኅበዝ ይህ ትግል መጥራት አለበት። አፍርሶ ጀማሪ የሆኑትን አንጃዎች ከወያኔ መሳሪያነት ነጥለን ማየት የለብንም። ዛሬ አንጃው ከኢሕአፓ ሲታገል ኢሕአፓ ግን እንደ ጥንቱ ከህዝብ ጋር ሆኖ ወያኔን በመፋለም ላይ ነው ያለው። ይህን ትግል ቀልባሽ የሆነውን አጥፊ የባንዳ ቡችላ የሆነውን አንጃ ከሕዝብ መነጠሉ ወያኔ ላይ የምናውለውን የትግል ሃይላችንን ብርቱ ያደርገዋል። ይህ በአንጃዎች የተበከለው ትግላችን መጽዳት አለበት። ወያኔን ካንጃ አንጃውን ከወያኔ ነጥለን አንመልከት። ሁለቱም ለህዝባዊው ትግለ መሰናክል ናቸው። አንጃዎችን ከመታን ወያኔን ለመምታት አይከብደንም። ልብ ይበሉ በጣር ላይ የነበረው ወያኔ እድሜ ለነልደቱ ነብስ ሊዘራ ችሏል። ዛሬ ደግም የወቅቱ የቅንጅትና የኢሕአፓ አንጃዎች ወዝ ያጣውን ወያኔ ሊያሳምሩትና የህዝቡን ሰቆቃ ሊያራዝሙት ደፋቀና እያሉ ስለመሆኑ የሚሰማ ጆሮ ይስማ የሚያይ አይን ይይ። ኅበዝ ይህን የህዝብ ትግል ከአንጃ በማጽዳት ፈር እናሲዘው።

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

ይህ የሕዝብ ትግል ይጠራ ዘንድ በቅንጅትም ሆነ በህብረቱ ላይ እየታየ ያለውን ጨርቁ ጨርቅ ላይሆን የመለጣጠፍን የመደረት ሙከራ ውኃ ቅዳ ውኃ መልስ ነውና ባስቸኳያ መግታት አለበት። ትግላችንና ድርጅቶቻችን የተሃድሶ ለውጥ ያሻቸዋል። ከመካከላችን አንጃዎችንና ባንዳዎችን ማጥራት ብቻ ሳይሆን እያንዳንዳችንም ከራሳችን ለለውጥ መዘጋጀት አለብን። መተቸት ግን ተገቢ የሆን ትችት(ሂስ) የሚደገፍ ቢሆንም ለሚቀርበውም ሂስ ተቀባይ አእምሮ ሊኖረንም ይገባል። ሳበዝ አሰ ገሰሱም በሙሉ ስለተሰባሰበ የቅንጅት ወይም የህብረት ትግል የተሳካ አይሆንም። ትግሉ እንዲሳካ እውነተኛ የህዝብ ወገኖች የተጠናከረ የጋራ ትግል ይጠበቅባቸዋል። እኔ ትግሉን ካልመራሁት አንጃ እፈጥራለሁ ባዮችን መለየት እንክርዳድን ከጥሩ ዘር የመለየት ያህል ቀላል ነው ትኩረት ከሰጠነው። ሳብዝ ይህ የህዝብ ትግል መጥራት የግድ አለበት!!

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com